# የዮዲት ዲቃላ

እነ ሱሪ ባንገት ፤ ካልወለቀ ባዮች
ለዋርካው ለዛፉ ፣ ለኩሬው ሰጋጆች
የይሁዳ አጋር ፤ የናት ጡት ነካሾች
ሞትን የሚጠሩ ፤ የሲዖል ወዳጆች
የጨለማው ልዑል ፤ የሳጥናኤል ልጆች
ትንቢት መፈፀሚያ ፤ የገሃነም ደጆች ።

አብይ በለው ለማ ፣ ሽመልስ ታከለ
አረም አሜኬላ ፣ ባገር የበቀለ
ትንንሽ ጭንቅላት ፣ ክህደት የተሞሉ
ኑፋቄ አስተማሪ ፣ ካምላክ የተጣሉ
የፋኝት ልጅ እባብ ፣ የእምነት አሜኬላ
ሰው የተመሰሉ ፣ የዲያቢሎስ ጥላ ።

ልክ እንደ ይሁዳ ፤ በሹክሹክታ መክሮ
ቀኖና ዶግማዋን ፣ ስርዓቷን ሽሮ
ኑፋቄን ሊያስፋፋ ፣ ተዋህዶን ቀብሮ
ሊገባ ይዳዳል ፣ ቅጥሯን ተሻግሮ
መቼ ይደፈርና ፤ በመቤቴ ታጥሮ ።

ለሰላም ተብሎ ፣ እነሱን ባዘለች
እሾህ ኩርንችቶች ፣ የገሃነም ደጆች
በጫጫታ አምላኪ ፣ የመድረክ ደናሾች
እንዳበደ ውሻ ፣ ያዩትን ነካሾች
የጨለማው ንጉስ ፣ ደቀመዛሙርቶች
የሞት ሃዋርያ ፤ ምግባረ አርዮስ
ደፋ ቀና ይላል ፤ ተዋህዶን ሊያፈርስ ።

ከላይ ታች ቢሉ ፤ ዙሪያውን ቢሮጡ
ጺዮን ላይ ቢነሱ ፤ ሰው ቢበጠብጡ
አስሩን ቢጭሩ ፤ ሺውን ቢቧጥጡ
ሆድ ሲያውቅ ዶሮ ማታ ፤ ጉልበትን መጨረስ
ኦርቶዶክስ እንደሆን ፤ እስከ ምፅዓት አትፈርስ
ትኖራለች እንጂ ፣ ዘወትር ስትወደስ
ታብባለች ገና ፤ በዓለም ላይ ልትነግስ ።

የገሃነም ደጆች ፧ ሊያጠፏት ቢያልሙ
በሚችሉት ሁሉ ፧ ቢለፉ ቢደክሙ
ጌታ በመስቀሉ ፧ ያቆማት በደሙ
ቃሉ ቃል ናትና ፧ አይፋቅ ማህተሙ
ተዋህዶ አትጠፋም ፧ እስከ ዘላለሙ
አይርፈድባችሁ ፤ በጊዜ ታረሙ
    የግራኝ መሀምመድ ፤ የዮዲት ዲቃላ
    የአረብ ተላላኪ ፤ የመንደር ቡችላ
    ጥጋብ አያዋጣም ፤ ታለቅሳለህ ኋላ ።

ታዛቢው

Septmber 3/2019